## <u>ገቡ ወደ ማጡ</u>

በምስራቅ በሐረር፤
በኦጋዴን ድንበር፤
በጎዴ በዋርዴር፤
ታቹን ደገሃቡር፤
መሬቱን ሲቆፍር፤
ሲለፋና ሲጥር፤
በሐሩር እና ቁር፤
ሜዳውን ሲጫጭር
ኢትዮጵያዊው ምሁር፤
ደግሞ ያ ላብአደር።

ለእማማ ኢትዮጵያ፤
ማጌጫ መታያ፤
ድህነት መቅበሪያ፤
ለዜጎቿ መኩሪያ።

በማለት ሲጣጥር፤
በአሸዋው በቆንጥር።

እዛው በተኛበት፤
በጣጥሰው ሲጥሉት፤
ሲያቆስሉት ሲገድሉት፤
ደጋግመው በጥይት፤
በሳንጃ ሲወጉት፤

በደም የሰከሩ፤
በሬሳው ሲያቅራሩ፤
“ፍትህ” ሲዘምሩ
ሬሳ እየዞሩ፤
ደግሞ ሲጨፍሩ፤
ሲያወኩ ሲያወሩ!!

ፊታቸው ሲፈካ፤
ነፍሳቸው ስትረካ፤
ስጋቸው ሲመካ፤
በበረሐው ጫካ፤

ዙሪያ ገቡ ሁሉ፤
ተውጦ በጽልመት፤
ተከቦ እንዳመሉ፤

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በሙታን መላእክት፤
በጋራ በህብረት፤
ዜማ ሲያወርዱበት።

ሲሰማ ሲደመጥ፤
እሪታ ጻረሞት፤
የጥላቻ ረመጥ፤
ያልተሟሸ ዋሽንት፤
ያልሰከነ ጩሁት፤
በሙታን መካከል
በጻረሞት ክልል፤
ሊታወጅ “ነጻነት”።

በሬሳው “ነጻነት”፤
ቆመው ሊያውጁበት፤
በቆፈረው መሬት፤
ዘይት ባወጣበት፤
እሳት ሊያነዱበት።

ውጉዝ ከአርዮስ፤
እንደማለት ፋንታ፤
መረ’ገም መ’ኮ’ነ’ን ፤
የጎጥን በሽታ፤
ጥቁር ውሻ ይውለድ፤
እንደ ማለት ፋንታ፤
በለቅሶ ይረገድ፤
ይገለጥ በእሪታ፤
እንደ ማለት ፋንታ……

ኑባሬ ህግጋት ፤
መሆኑን ሳያጡ፤
ተጣድፈው ያሰሩት ፤
ሊፈታ ሲሮጡ፤
በፊርማ በሰነድ፤
ሲገቡ ከድጡ፤
ዝምታን በመምረጥ ፤
ገቡ ወደ ማጡ!!!

ጋምቢ-ኦቶ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com